# ምን ያልተባለ ነበር ?-- ሰሚ ጠፋ እንጂ፤ ዋሾ በረከተ እንጂ!

## ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሬዲዮ ወቅታዊ ሐተታ

ዓመት አልፎ ዓመት ሲተካ ታሪክ የተደጋገመ ቢመስልም ቧልትነትን ትቶ ምጸትነትን ማቀፉ ደግሞ ታሪካዊ ሀቅ ነው። የወያኔ አገዛዝ ካለፈው ቢመሳሰል፤ በድርጅቶች ላይ የተነሱና እየተነሡ ያሉ የፖለቲካ ጊንጦች ያው አንድ መስለው ቢታዩ የሚያስገርም አይደለም። ታሪክ ራሱን ይደግማል -- ዛሬ ከትላንት አንድ ነው፤ ያው ነው ማለቱን ባንችልም። መሰረታዊ በሆኑት የሀገራችን ጉዳይ ላይ ዛሬ ወያኔና ቅጥረኞቹ የሚረባረቡበት፣ ኢሕአፓ ከዓመታት በፊት ያሰራጨውን መልዕክቶች ማቅረቡ ወቅታዊ ነው ።

ዴሞክራሲያ ገና በ1966 ሲጽፍ የነበረውን ቀደም ብለን በየጊዜው አቅርበናል። ቀጥሎም ሕዝብ ለፋሺስታዊ አፈና ተሸናፊ እንዳይሆን፤ ለወያኔ እጅ እንዳይሰጥ ያኔም የተባለው ለዛሬም የሚሰራ ነውና እነሆ -- ዴሞክራሲያ ቅጽ 14 ቁጥር አንድ (የካቲት 1980 ዓ.ም.) ይህን ማስጠንቀቂያ አቅርቦ ነበር፡

“ለውጥ ይመጣል -- ያ ለውጥ ግን ሐዲዱን እንዳይስትና እዚያው ከዳከርንበት የተለመደ አዘቅት ክትቶን “ያንኑ ያንኑ እንዳንጫወተው” አሁን ባለው መሪር አገዛዝ በመንገሽገሽ ብቻ ከዚህ የባሰ አይመጣም፤ የመጣው ይምጣ በሚል ደርግ በላባደሩና በሰፊው ሕዝብ ልዕልና ሲምል ሲገዘት እንደነበረው፤ ሌላ አንጃት የሚበላ መሐላ ይዘው አንደበታቸውን አለስልሰው የሚቀርቡ ስለ ነጻነት ስለ ፍትሕ ርትዕ የሚያንበለብሉ የዴሞክራሲ ነቢያት ዳግመኛ ሊያማልሉን አይገባም።

በሕዝብና በፖለቲካ ስልጣኑ መካከል አጋፋሪ፤ አማጭ ረማጭ፤ የነገር አባት፤ ስማ በለው፤ አስተርጓሚ አያስፈልገውም። ጭቁኑ ሕዝብ በስልጣኑ ላይ ከራሱ በስተቀር ሌላ ነቢይ፤ ሌላ መሲሕ አይፈልግም። እኛ ሞግዚት እንሁንህ፤ እኛ እንወቅልህ እያሉ የህዝብን ትግል መሰላል አድርገው ከስልጣን ኮርቻ ላይ የወጡ ሁሉ የራሳቸውን መደብ አጠናክረው ሰፊውን ሕዝብ መጋለቢያ፤ ሀገርን የጥቅማቸው መለወጫ ከማድረግ የተቆጠቡበት ታሪክ አልታየም። … ይህ የመርገም ምዕራፍ ዳግመኛ እንዳይገለጥ ለመጨረሻ ጊዜ ታጥፎ ገሀነም መውረድ አለበት።”

ይህ ማስጠንቀቂያና ምክር ሰሚ አጥቶ ደርግ በወያኔ ሲትካ በርካታ ዜጋ የተሻለ መጣ ብሎ ተደናግሮ ለወያኔም ጊዜ እንደሰጠ ያየነው ነው። ዛሬም ወያኔ ወደ ውድቀቱ በሚያመራበት ወቅት የባስ እንዳይመጣ የሚለውን ከወያኔ አስወጋጁ ትግል ጋር አያይዘን ማስኬድ አለብን። ወያኔ እኔ ከተወገድኩ ሀገሪቷ ትጠፋለች ብሎ የሚያቅራራው ለራሱ ጥቅም ቢሆንም የዛሬው ትግል የነገን ድልና ግብ ከግንዛቤው ማራቅ አይችልም። ዴሞክራሲያም ይህን ሲያሰምርበት ሲያስረዳ የሚከተለውንም ጽፎ ነበር።

“የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎት ከአንድ ጌታ ተላቆ ለሌላ ጌታ ማደር አይደለም። የፊውዳሉ ስርዓት ልውደቅ ልውደቅ እያለ ሲርገደገድ በትር ምርኩዝ ሆኖ አዘባንኖ ያቆየው የአሜሪካን ኢምፔርያሊዝም እንደነበር ግልጽ ነው። በ እግሩ የተተካው ፋሺስታዊ ደርግ ሶቭዬት ኢምፔሪያዝምን ጥላ ከለላ አድርጎ፤ ባስተማረው የአፈና ጥበብ ነው ከመምህሩ ደቀ መዝሙሩ ባስናቀ ሁኔታ አምቆ ይዞ እየገዛ ያለው። የአፍሪካ ቀንድ ካላት ስትራተጂያዊ አቀማመጥ የተነሳ ሃያላን መንግስታት መራኮቻቸው እንዳደረጓት ነው ። የኔ ሰበካ ትሁን፤ የኔ ሰበካ ትሁን ፉክክራቸው በዚህ አካባቢ ባሉት ሕዝቦች ነጻነት ላይ የተንጠለጠለ ሠይፍ ነው።

ማንም ማን ተእንግዲህ በነጻነትና በዴሞክራሲ ሽፋን ከበስተጀርባው "ባዕድ አምላክ" አድራጊ ፈጣሪ ጌታ አለማስከተሉን ዓይን አፍጦ ማየትን ይጠይቃል። የኢትዮጵያ ህዝብ ዝንተ ዓለም የፖለቲካ የኤኮኖሚ ገባር ሆኖ አጥንት ጉልጥምቱን አስገዝቶ የድህነት መለኪያ ሆኖ መኖሩ እዚህ ምዕራፍ ላይ ማብቂያው ይሁን። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሌላ ጌታ ቀይሮ ዕድሉን ማየት አይደለም የሚፈልገው። የኢትዮጵያ ሠፊ ሕዝብ የሚፈልገው ራሱ የራሱ ጌታ መሆንን ነው። ራሱ በዕድሉ ላይ ወሳኝ ሆኖ ከሃሊነቱን ማሳየት ነው -- በራሱ ትግል ራሱ ተዋናይ ሆኖ የፈጠራ ችሎታውን ማሳየት ነው -- ከቶውንም የሰው እጅ ማየት አንገሽግሾታል። ተእንግዲህ በገዛ ዳቦው ልብ ልቡን ሊያጣው አይፈልግም።"

በአሁኑ ጊዜ ሁሉም ዜጋ የሚያውቀው ሀቅ አሜሪካ፣ አውሮጳና ቻይና የዘረኛው አገዛዝ ደጋፊና ተንከባካቢ ሆነውና የህዝብንም ትግል ተጻርረው እንደቆሙ ነው። የህዝብ ትግል ይህንን ሀቅ ቸል ሊለው የሚችል አይደለም። በገንዘብ ሀይል ሀያል ነን ብለው የተነሱትና የሕዝብን ትግል በማፈን የተካኑት እነ ካታርና ሳውዲ አረቢያም የሚረሱ አይደሉም። አሜሪካ በርካታ ዜጎችን በቅጥረኝነት መልምላ -- በተለይም በአሜሪካ -- ምሁር፣ ጠበብት፣ ጋዜጠኛ ወዘተ በሚል ሽፋን ታጋይ ሀይሎችንና ሀገር ወዳድ መሪዎችን በማጥቃትና ወያኔን በማገዝ ላይ ናት። ኢትዮጵያን የሚቀራመቱት ባዕዳን የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስቀድምን ታጋር ድርጅት አይፈልጉም። የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ይከበር የሚለውን ድርጅት ይጠላሉ። ለስልጣን እንዳይደርስም ሙሉ ጥረት ያደርጋሉ። ዛሬ በአንዳንድ ድርጅቶች ላይ የተጧጧፈው አፍራሽ ዘመቻ ጀርባ ወያኔ ብቻ ሳይሆን አሜሪካና እንግሊዝ አሉበት። ይህም ጉዳይ የሕዝብና የታጋዮችን ትኩረት መሳብ ይገባዋል -- ለባዕዳን ሴራ ሰለባ ሆነን ዳግም ሀገራችንን ለከፋ አደጋ እንዳናጋልጥ።

ለባዕዳን ጸረ ኢትዮጵያ ዘመቻ አመቺ መሳሪያ ሆነው የሚገኙት የግንጠላና የጥላቻ አቀንቃኞች ናቸው። በቅርቡ ቡችላቸው በሆነና አዋቂ ብለው በሚያራግቡለት ግለሰብ አማካይነት የሙስሊሙን እንቅስቃሴ ለመከፋፈልና ሕዝብንም በርስ በርስ ጥላቻ ለማፋጀት የተደረገ ሙከራ ምሳሌ ነው። የግንጠላን ጎጂነት በመልዕክተ ኢ.ሕአፓ ህዳር 1984 የሚከተለው ሰፍሮ ነበር፡

"ጠባብ አመለካከት ላይ የሚዳክሩ ሀይሎች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብትን በዓብይ መልኩ " የመገንጠል መብት" አድርገው እየወሰዱ "መገንጠል " ለሚሉት ብቻ ጫናና ቅድሚያ በመስጠት መፍትሔው መገንጠል ነው የሚል አቋም ይገፋሉ ። (ወያኔ በመጀመሪያ ) ፕሮግራሙ ሁሉም ብሔሮች ተገንጥለው የይራሳቸውን ነጻ መንግስታት ማቋቋም አለባቸው ይል የነበረው ለዚህ ነው። መገንጠል እንደ ብቸኛ አማራጭና መፍትሔም በመወሰዱ ይህን እርምጃ ተገቢ ነው ለማሰኘትም ስንኩል ምክንያቶች ( ቅኝ ግዛት፤ የማይታረቅ ቅራኔ፤ ወዘተ) ተደርድረዋል፤ ዛሬም እየቀረቡ ናቸው ።..... በዚህ መልክ ሆነ በሌላ ቢቅርብም ጠባብ ብሔረተኛ ስሜት ክትምክህት ባልተናነሰ ጎጂና አበጣባጭ በመሆኑም የመገንጠል መብት በዋናነት መራገቡ አንድነትን ሳይሆን እስከ ጎጥ ደረጃ ድረስ ብጥብጥንና ክፍፍልን እንደሚያመጣም ዛሬ በዓይኖቻችን ማየት የጀመርነው ሀቅ ነው።"

ኢ.ሕአፓ በዚህ መልክ የጠባብነትና ግንጠላን አደጋ ሲያጋልጥ ዛሬ ድርጅቱን የሚከሱት ክፍሎች በአብዛኛው ደረጃ ከወያኔ ጎን ተሰልፈውም ነበር ማለት ይቻላል። እንቀጥል። መልዕክተ ኢ.ሕአፓ ይህንንም ብሎ ነበር--

"ኢትዮጵያ የቆየ አንድነቷ የሁሉም ሕዝብ መራራ ትግልና ጠንካራ ፍላጎት ውጤት እንደመሆኑ መጠን የሚያኮራ ጸጋ እንጂ ችግሯ አልነበረም። አንድነቷ በእኩልነትና በዴሞክራሲ ላይ ተምስርቶ ይጠንክር ማለት ተገቢ አቋም ሲሆን አንድነቷ ለሕዝቦቿ መከራ ምክንያት የሆነ ይመስል መገነጣጠሏን እንደ

መርህና ዓላማ መውሰድ ግን አጥፊነት ከመሆን ሌላ ሊሆን አይችልም። ትኋን ለመግደል ቤት ማቃጠል፤ ጫማ ሲጠብ እግር መቁረጥ ነው የሚሉ ክፍሎች ግን አንድነትን የሚሸረሽሩትን ክስተቶች በማስወገድ አንድነትን ከመገንባት ይልቅ ሀገር ማፈራረስን ይመርጣሉ። የዚህ ውጤቱ ምን እንደሚሆን ደግሞ መታየት ጀምሯል። ለማንም የማይበጅ መፋጀት ነው።”

የሕዝብ ማፈናቀልን መስፋፋት ነው። በደኖ፤ ወተር፤ አርባጉጉን በሀገር ሁሉ ማስፋፋት ነው። የግንጠላ መንገድ ለባዕዳን እንደሚያመች የግብጹ አገዛዝ ኢትዮጵያን ለማጥቃት እንገንጠል የሚሉ ድርጅቶችን እናስታጥቅ ማለቱን ያስታውሷል። ለዚህም ነው ለግንጠላ አቅንቃኞች ጭምብል ለጋሽ ሳንሆን ማንነታቸውን እያጋለጥን መስመራቸውንም እንዲቀይሩና በኢትዮጵያ ኣንድነት ስር ለመብታቸው ይታገሉ ዘንድ ጥሪ ማቅረብ፤ ግፊት ማድረግ የሚገባው። ወያኔ የከተበውን አንቀጽ 39 መደገፍና ማወደስ ሳይሆን ይሰረዝ ዘንድና ከወያኔ ሰነድና አገዛዝ ጋር ወደ ትቢያ እንዲጣል መታገል ይገባል እንጂ ወያኔ ለራሱ የትግራይን መገንጠል ርኩስ አላማ ያዘጋጀውን መቀበል ስህተት ነው። ታሪካችንን ከመረመርን ደግሞ ጣሊያንም ሆነ እንግሊዝ በብሄረሰብ ደረጃ ከፋፍለው ሊገዙን ሞክረው ነበር። ወያኔም በውድቀቱ ወቅት ይህንኑ ስሜትና አቅዋም ተጠቅሞ ኢትዮጵያን ከፋፍሎ ሊጎዳ የሚታወቅ እቅድ አለው።

እንደገና እንደገና የትግላችንና የመስዋዕትነታችንን ፍሬ እንዳንቀማ ነቅተን መገኘት አለብን። ደርግ ነጠቀን፤ወያኔ ነጠቀን። ነገ ደግሞ ጭምብል ያጠለቀ ሌላ ወያኔ ወይም የባዕዳን ቅጥረኛ  በትግላችን ተጠቅሞ ስልጣን እንዳይዝ መከላከል አለብን። ኢሕአፓ የሕዝብን ትግል ፍሬ አላስነጥቅም ብሎ ሲታገል የታየ ነውና ከወዲሂ ድርጅቱን ለማዳከም፤ ለመከፋፍል፤ ለመበተንና አመራሩንም ለማጥቃት ዘመቻው ተጧጡፎ ይታያል። ዜጎች ሁሉ ይህ ህዝብን

ለመጉዳት የተጠነሰሰ ጸረ ኢሕአፓ ዘመቻ እንዲከሽፍ ከድርጅቱ ጎን መቆም አለበት። ከዴሞክራሲያ ጠቅሰን እናጠቃል፤

“ይህች ሰዓት ለኢትዮጵያ ህዝብ ወሳኝ የጽሞና ሰዓት ናት። ሁሉም በየበኩሉ የሚመኛት ኢትዮጵያ ትኖረዋለች። ግን እንደ እያንዳንዱ ግለሰብ፤ ቡድን፤ ወዘተ ምኞት ልትሰራ፤ ልትስተናበር አትችልም፡፡ አንዱ በሌላው ላይ የራሱን ምኞት ለመጫን ሲነሳ የተጫነበት ሁሉ በጀ ሊል አይችልም። አልጫን ያለውን የተባለ የአስተሐቅሮ ስም ስላወጡለት ፤ የተባለ ውግዘት ስላወረዱበት፤ ጦር ስለመዘዙበት፤ ያችን የተመኟትን ሀገር መመስረት አይቻልም። በዚህ መንገድ ተሂዶ መንግስት የሚረጋ፤ አልጋ የሚጸና ቢሆን ኖሮ የፋሺስታዊው መንግስት ኢትዮጵያ የትና የት በደረሰች ነበር። ሀገር የጋራ ናት ሲባል እያንዳንዱ እንደ ግል ምኞቱ የሚስላት የሚኳላት ሀገር ሳትሆን የብዙሃኑን ምኞት የምታንጸባርቅ፤ የውሁዳኑንም የምትዘክር፤ ለሁሉም በረከት ረድኤቷ የሚደርስ ለማለት ነው። ራሳቸውን የብዙሀኑ ወኪል አድርገው ወይም ብዙሃኑን ሆነው፤ ይህ ነው የብዙሃኑ ድምጽ፤ ያ ነው የብዙሃኑ አቅዋም የሚሉትን ወይም በግርግም ውስጥ አጉረው እያስለፈለፉ በተደረገው “ነጻና ዴሞክራሲያዊ” ውይይት ሰፊው ሕዝብ ይህንን ወሰነ፤ ያንን አወገዘ.. የሚለውን ዓይነት እጅ እጅ ያለ ወዘበሬታ እዚህ ቁምነገር ወግ ውስጥ የምንዘንቀው አይሆንም”።

ሁሉም ዜጋ ለሚኮራባት ኢትዮጵያ በጋራ እንታገል!

የህዝብ ጎራ ከሰርጎ ገቦች ይጽዳ!!

ውድቀት ለወያኔ፤ ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

ነሐሴ 2005 ዓ. ም.